## EFF (የብዙ ፡ቋንቋዎች ፡ ተቋም)

- በመንግሥትና ፡ በግል ፡ ድርጅቶች ፡ ላይ ፡ ያተኮረ ፡ ነው።
- የእናት ፡ ቋንቋን፡ ትምሕርት፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ት/ቤት፡ እና በሁለተኛ ፡ ደረጃ፡ት/ቤት ፡ ላይ ፡ ይሰጣል።
- የማስጠናት ፡ ሥራ ፡ በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ አዲስ ፡ ለመጡ ፡ ተማሪዎች፡ ያግዛል።
- በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተማሪው ፡ ያለበትን ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ መገምገም ።
- አዲስ፡ለመጡ፡ተማሪዎች፡ በአማርኛ፡ቋንቋ፡ፈተና ፡ ይሰጣል ።

**Enheten för flerspråkighet**
flersprakighet@uppsala.se
018-727 20 26
Uppsala kommun

# የአፍ፡መፍቻ፡ቋንቋ፡ማስተማር፡፡




flersprakighet.uppsala.se

Uppsala kommun

## የአማርኛን ፡ቋንቋ፡ ማን ፡ ይማራል?

(ብሄራዊ አናሳ ቋንቋዎችን ፡ አይመለከትም)

የአንድ ፡ ተማሪ ፡ ወላጆች፡ ከልጁ ፡ አፍ፡መፍቻ፡ቋንቋ፡ ከስዊድኝና፡ የተለየ፡ ቋንቋ፡ የሚናገር ፡ ከሆነ፡ እንዲማር ፡ የሚመቻቹለት ፤ መሥፈርቶች።

፩. ልጁ(ተማሪው)ቤት ፡ውስጥ፡ቋንቋውን፡የሚናገር ፡ ከሆነ።

፪. ልጁ ፡ መሠረታዊ፡ የሆነ፡ የቋንቋ፡ዕውቀት ፡ ሲኖረው።

ተማሪው ፡ቋንቋውን፡ መናገርና፡ መረዳት፡ የሚችል፡መሆን ፡ አለበት ። ትምህርቱ፡ በአማርኛ ፡ ቢሰጥም፡ የሃገሪቱን፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥ፡ ሕግ ፡ የሚከተል ፡ ይሆናል።

## ብሔራዊ ፤ አናሳ ፡ቋንቋዎች።

ስዊድን፡ የሚከተሉት፡ አናሳ ፡ቋንቋዎች፡ አሏት፥

ፊኒስካ ፣ ሚያንኬሊ ፣ ሳሚስካ ፣ሮማኒ ፣

ጂዲሽ።

አናሳ ፡ ቋንቋዎችን፡ ለመማር፡ የአናሳው ፡ ቋንቋ፡ ጎሳ ፡ መሆንን ፡ ይጠይቃል። ተማሪዎች ፡ ቤት ፡ቋንቋውን፡መናገርና፡የቋንቋው፡ መሠረታዊ፡ ዕውቀት፡ እንዲኖራቸው፡ አይገደዱም። ሁለት ፡ የኮርስ ፡ ዕቅዶች ፡ አሉት ፡ ተማሪው ፡ እንደ ፡ ቋንቋው፡ተናጋሪና፡ ብሎም፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ጀማሪ፡ ሊመዘገብ ፡ ይችላል።

የብዙ፡ ቋንቋዎች፡ተቋም (EFF) የአፍ፡ መፍቻ፡ቋንቋ ፡ ትምህርት ፡ ኡፕሳላ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሰጥ ፡ ያመቻቻል።

### መሠረታዊ፡ የሆነ፡ቋንቋ፡ ዕውቀት

ከአናሳ ፡ቋንቋ፡ በስተቀር ፡ በሁሉም ፡ቋንቋዎች፡መሠረታዊ፡

የቋንቋ፡ ዕውቀት ፡አስፈላጊ ፡ መመዘኛ ፡ መሆኑን ፡ ያስገነዝባል።

መምሕሩ ፡ ተማሪውን፡ ማስተማር ፡ እንደጀመረ ፡ የተማሪውን፡ መሠረታዊ ፡ የሆነ ፡የቋንቋ፡ ዕውቀት ፡ አስቀድሞ፡ ይገመግማል። የተማሪው ፡ የማዳመጥና፡ የመናገር ፡ ችሎታው ፡ ይገመገማል። ስለ፡ መሠረታዊ፡ዕውቀት ፡ የበለጠ ፡ መረጃ ፡ ለማግኘት ፡ የብዙ ፡ቋንቋዎች፡ ተቋም(EFF) ድሕረ ፡ ገጽን ፡ ይመልከቱ።

### እንደሚከተለው ፡ያመለክታሉ

የተማሪው ፡ ወላጆች ፡ ናቸው ፡ ማመልከት ፡ ያለባቸው ። ቅጾቹ ፡ በየትምህርት ፡ ቤቱና ፡ የብዙዎች ፡ የቋንቋ፡ተቋም(EFF) ድህረ ፡ ገጽ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ። ቅጾቹን ፡ ይሙሉ ፣ ይፈርሙና ለ/ትቤት ፡ ይተዉ። የ/ትቤት፡ ርዕሰ ፡ መምሕር ፡ የገባውን ፡ ማመልከቻ ፡ ማጽደቅ ፡ አለበት ። ከዛ/ትቤቱ፡ ወደ ፡ EFF ይልከዋል።
የሚመጣው ፡ የትምሕርት ፡ ዘመን ፡

እ.ኤ.አ 15 juni ፡ ሲጀመር፡ከ 15 juni በኋላ ፡የሚሞላ ፡ ቅጽ ፡ ቦታ ፡ ለማግኘቱ ፡ ማረጋገጫ ፡ አንሰጥም።

## ትምህርቱ፡ እንደሚከተለው ፡ ይቀናጃል።

በኡፕሳላ ፡ የቋንቋ፡ትምህርት ፡ በተፈለገው ፡ ጊዜ፡ ለመስጠት ፡ማረጋገጫ፡ አንሰጥም፡ ፡ ትምሕርቱ ፡ ከመደበኛው ፡ ትምሕርት ፡ ውጭ ፡ ይሰጣል። አንዳንዴ፡መደበኛው ፡ትምሕርት ፡ እንዳለቀ ፡ ይሰጣል። ከF-5 ያሉ ፡ ተማሪዎች ፡ ትምሕርቱ ፡ በት/ቤታቸው ፡ ይሰጣቸዋል። ከ፮ እስከ ፱ኛ ክፍል ፡ ያሉ ፡ ተማሪዎች ፡ አንደ፡ ክፍል ፡ ደረጃቸው ፡ ተከፋፍለው ፡ አንድ፡ላይ ፡በአንድ ፡ በተመረጠ፡ ት/ቤት፡ ውስጥ ፡ ሰዓት ፡ ተለይቶላቸው፡ ከሰዓት በሁዋላ ወይም(በምሽት)፡ ከመደበኛ፡ትምሕርት ፡ ሰዓት ፡ውጭ፡ ትምህርቱ ፡ይሰጣል።

ተማሪው ፡ የተመደበበት ፡ ት/ቤት ፡ድረስ ይሄዳል ። ተማሪው ፡ የአውቶቢስ ፡ትኬት ከሌለው ፡ ከቋንቋ፡ መምሕሩ ፡ የአውቶቢስ ፡ ትኬት ፡ ይሰጠዋል።

## ለበለጠ፡ መረጃ

ከብዙ ፡ቋንቋዎች ፡ ተቋም፡ (EFF) ድሕረ ገጽ ፡ የበለጠ ፡ መረጃ ፡ ስለ ፡ ቋንቋ፡ ትምሕርቱ ፡ አሰጣጥ፡ ማግኘት ፡ ይቻላል።

flerspraakighet.uppsala.se

ENHETEN FÖR FLERSPRÅKIGHET